የሰበር መ/ቁ. 37573

ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት - ነ/ፈጅ አለምፀሐይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መሐመድ አደን - በሌሉበት

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ሠራተኛው መብቱን የሚጠይቅበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡

በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበታቸው ወደ ስራ ለመመለስ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪ በፈፀሙት ጥፋት ከስራ መሠናበታቸው በሕጉ መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤትም ስንብቱ ሕገ- ወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደስራቸው እንዲመለሱ አልያም ካሣ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ለዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ክሱ በይርጋ አይታገድም፣ ስንብቱም ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪም ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም ግንኙነት አይኖርም ተብሎ የሚገመትበት ምክንያት ስለሌለ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ ይመለሱ በማለት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ቅሬታውም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ሲሆን ክስ የመሠረቱት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም በመሆኑ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ይቋረጣል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን ጥያቄ ያልተቀበሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል የሠበር አቤቱታ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

እኛም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሣኔዎች እና ከሕጉ አኳያ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ ላይ እንደተመለከትነው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ነው በማለት አመልካች ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት ተቃውሞ የለም እንደዚሁም ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ ያቀረቡት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም መሆኑንም ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ ከተሰናበቱበት ቀን ጀምሮ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ እስከመሠረቱበት ጊዜ ድረስ ሲታሰብ ከ3 ወር በላይ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/2/ መሠረት ደግሞ ሠራተኛው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ስራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚቋረጥ ተመልክቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ፈጽመዋል በተባሉት ጥፋት ክስ ተመስርቶባቸው ሲጣራ ቆይቶ ፖሊስ ከወንጀሉ ነፃ መሆናቸውን ያረጋገጠው መስከረም 18/2000 በመሆኑ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ከዚሁ ቀን ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ

164 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆኑ ፍ/ቤቱ የገለፀው ሁኔታ ይርጋን ያቋርጣሉ ተብለው ከተመለከቱት ሁኔታዎች ስር የሚካተት አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪ በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ ነፃ መሆናቸው እስኪረጋገጥ ድረስ የነበረውን ጊዜ በይርጋ አቆጣጠር ጊዜ ውስጥ አይካተትም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም አልፎ አመልካች ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ እንኳን ሣይኖር ተጠሪውን በሚጠቅም መልኩ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ማሻሻሉ የዳኝነት አሠራር ስርዓት አለመከተሉን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ የተጠሪ ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ከ3 ወር በኂላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ይህ ታልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መሠጠቱ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0/21/200 በ28/2/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በአፋር ክልል የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0993 በ18/4/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ክስ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/2/ በይርጋ ውድቅ ሆኗል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ